ሕዝብ እንዲያውቀው፣

# የወያኔ ተለጣፊ ተቃዋሚ ቡድን ስብሰባ በለንደን፣




የወያኔ ተለጣፊ ተቃዋሚ በመባል የሚታወቀው፣ የልደቱ ቡድን፣ መጭውን የወያኔ ምርጫ ለማዳመቅ ከወያኔ በደረሰው ትዕዛዝ መሰረት፣ በሐገሩ ውስጥ ለሚያደርገው ማጭበርበር ይረዳል ብሎ በማሰብ በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጱያዊያንም ጋር ግንኙነት ያለው ለማስመሰል፣ በወያኔ በተያዘለት ባጀት እና በወያኔ ኤምባሲ በሚደረግለት ትብብር፣ በለንደን ከተማ የድብቅ ስብሰባ እያዘጋጀ መሆኑ ሲታወቅ፣ በዚህም ስብሰባ ላይ የሚገኙት በጣት የሚቆጠሩ የተለጣፊ ተቃዋሚ ተለጣፊ ደጋፊዎች፣ ቁጥር አንዳያንስ በመፍራት በለንደን የሚገኙ የወያኔ ቡድን አባላትና ደጋፊዎች በስብሰባው ላይ ተገኝተው የተሰብሳቢውን ቁጥር እንዲያበራክቱ ትእዛዝ የተላለፈላቸው መሆኑ በተጭማሪ ታውቋል።

የልደቱ ተለጣፊ ተቃዋሚ ቡድን ደጋፊዎች፣ አሁንም ያልተረዱት አንድ መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር፣ ሕዝብ በአደባባይ የሰጠውን ከፍተኛ ዕምነት መሽከም አቅቶት፣ በሆነ ባልሆነው ለዘረኛ አምባገነን ቡድን መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍርፋሪ በመንበርከኩ፣ ሕዝቡ የሞራል ፍርድ በማሳረፍ፣ በየስርቻው ለመሽሎክሎክ ያስገደደውን፣ ከፍተኛ የሞራል መመዘኛ ያለውን፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እውነታን ነው።

ከዚህ እውነታ ውጭ የሕዝብን አይን ፍርቶ በየስርቻው የሚደረገው ውጣ ውረድ፣ ለጥቂት የተለጣፊው ተቃዋሚ ቡድን መሪዎች ያለን የሎሌ፣ ጭፍን ታማኝነት ከማረጋገጫ አጋጣሚ ከመሆን አልፎ፣ ሕዝባዊና ሐገራዊ ፊይዳ ይኖረዋል ብሎ ማሰብ ትርፉ ድካም ነው።

አንተነህ ከለንደን